## KeNahom Mann'nnetu KeTefabet yetelake i-Tomar I:-

Letewededu Nebure-ed Ermias Kebede፡

Be erso bekule yetesafut yeMenfes Qidus metsahftochene begebeya selatahwachew endet endemagegnachew yigelisulegne zend bethtena etayikalehu.

Nahom Manenetu Ketefabet.

## LeNahom Mann'nnetu KeTefabet i-Tomar I yeteseTe Mels:-

Y'dres be'Igziabher s'm letewededu wendmei Ato Nahom:

Innatach'n ItyoPya behonech'w, beQ'dst D'ng'l Mariam s'm selamtayen aqerb'll'wotallehu.

*"Be erso bekule yetesafut yeMenfes Q'dus metsahftochene begebeya selaTahwachew endet endemagegnachew yigelisulegne zend bethtena etayikalehu!"* blew letsaful'gn debdabewo, Igzer ysT'll'gn!

Kes'ra bzat inna yeh'wa mesmer lemag'gnet kegeTemegn ikk'l yetenessa, y'h melsei eskahun bemezegyetu, asqedmei y'qrta idiadergul'gn ilemm'nallehu.

Kenebbarochu inna begebeya lay kemay'gegnut metsah'ftach'n mekakel, "ItyoPya: ye'Alemu Meffareja", "ItyoPya Inna ItyoPyannet: 1gna MetTs'haf"; degmom, "Addam inna Hewan: be'ItyoPya! 2gna Mets'haf" yetebalut sostu mets'hafoch, indegena lehuletegna gize tat'mew semonun le'anbabiwoch iyeteseraCHu nachew; inna beqellalu liagegnuachew ychalwotal.

Iskeziaw'm mnalbat kasfelegewo:

1gna, le'ahunu beKiss-S'lkoch quT'r: 0944-1023-68; 0911-6844-52; 0912-9371-85; beBet-S'lkoch quTr: 011-4-1618-85 enna 011-3-2000-85;

2gna, lewedefit'm, iskahun yetatemut'n'm hone, yemmittattemut'n metsah'ft lemag'gnet, le'Akkefafay Wekkillach'n: leWashera Metsahft Bet, beKiss-Slk: **0911-6352- 25 inna 0910-9249-71 beqeT'ta medewel y'ch'lallu.**

**"Mann'nnetwo yeTefabb'wot Nahom"** irswo kehonu, "ItyoPyawiw: beMann'nnetu F'llegan inna lelochun, beItyoPya: ye'Igziabher Meng'st wsT yetattemut'n inna yemmittatemut'n Mets'hafoch, indih iyyefellegu yemmianeb'bu kehone, be'irg'T **"yeTefabb'wot'n Mann'nnetwon mell'sew yagegnu, Tenq'qew'm yawwequ Nahom y'honalu!" S'lezzih ijj'g dess y'belwot!**

Kidanawi Ermias Kebede Welde-Iyesus, [N'bure-Id ze'Aksum Tsyon].

## ከአቶ ናሆም የቀረበ፡ የእ-ጦማር ፪ኛ የመልስ ጥያቄ፡-

*በመጀመሪያ፡ ስለአበረታች ምላሽዎ፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።*
*እኔ፡ ገና ጉርምስና ዕድሜ ላይ ስለኾንኩ፡ "አንተ!" ቢሉኝ፡ ደስ ይለኛል።*
*መጽሓፍ ካነበብኩ በኋላ፡ ጥያቄ መጠየቅ እችላለሁ ወይ?*
*ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም ትስጥልኝ!*

## ለአቶ ናሆም የእ-ጦማር ፪ኛ የመልስ ጥያቄ የተሰጠ፡ ፪ኛ መልስ፡-

ይድረስ፡- ለተከበሩ ወንድሜ አቶ ናሆም!

በእናታችን ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም ስም፡ ሰላም እልዎታለሁ።

የጻፍሁልዎ እ-ጦማር፡ አበረታች ኾኖ ያገኙት መኾንዎን ስለገለጸልኝ መልስዎ፡ እግዜር ይስጥልኝ! በዚሁ መልስዎ፡-

፩ኛ፡ *"ገና በጉርምስና ዕድሜ ላይ ስለኾንኩ፡ 'አንተ' ቢሉኝ ደስ ይለኛል።"* ላሉት፡ "አንተ" የምልዎ፡ በእግዚአብሔራዊው ሥርዓታችን መሠረት፡ በኢትዮጵያዊው ቀዳማዊ መልከ-ጼዴቅ ቃል-ኪዳን ያገኙትን፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ኢትዮጵያዊነትዎን፡ በእግዚአብሔር እውነት እና በመንፈስ-ቅዱስ አምልኮዎ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ መንበር ፊት ቆመው፡ በእነርሱ የተቀዳጁትን የዘለዓለም ኪዳነ-ምሕረት ያተሙበትን፡ የቅዱስ ሥጋ እና የክቡር ደም ቁርባንን መቀበልዎን፤ እንዲሁም፡ በኖኅ ቀስተ-ደመና፡ የቃል-ኪዳን መታወቂያዎ የኾነውን፡ የሰንደቅ-ዓላማችንን ማተብ፡ በአንገትዎ በማሰር፡ የቃል-ኪዳን ምስክርነትዎን የሰጡ መኾንዎን ሲያረጋግጡልኝ ብቻ ነው፤ አዎን! ከዚያ በኋላ ነው፡ "አንተ" የምልዎ።

፪ኛ፡ *"መጽሓፍ ካነበብኩ በኋላ፡ ጥያቄ መጠየቅ እችላለሁ ወይ?"* ላሉት፡ መልሴ፡- "አዎን! ይችላሉ!" ነው። ነገር ግን፡ የጥያቄዎችዎ መልሶች ኹሉ፡ እዚያው መጻሕፍቶቼ ውስጥ ያሉ ስለኾኑ፤ ከእነርሱ የቀሩ ቢኖሩም እንኳ፡ በጎዋ-ሰሌዳችን፤ በዩቲዩብ እና በፌስቡክ፤ በሌሎቹም የጎዋ አውታር መድረኮቻችን ላይ ተመዝግበው ስለሚያገኟቸው፡ እነርሱን እየከፈቱ በማንበብ፡ ለቀሩት ጥያቄዎችዎ ኹሉ፡ በቂ የኾኑትን መልሶች ይመለከታሉ።

ስለዚህ፡ በዚህ ምክንያትና በዚያን ጊዜ፡ "ወደእኔ፡ ምንም ዓይነት ጥያቄን ማቅረብ የሚያስፈልግዎት አይኾንም!" ማለት ነው። ምናልባት፡ ከእነዚህ ኹሉ የጥያቄዎች መልሶች ያለፈ፡ አዲስ ጥያቄ ቢኖርዎት፡ ያን፡ ሊያቀርቡት ይችላሉ።

የኢትዮጵያ፡ እግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ፡-
ኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ [የአኵስም-ጽዮን፡ ንቡረ-እድ]።